የቤት ንብረት በእጅ መያዝን አስመልክቶ የተረጋገጠ ክስ -- ቅጽ (ፎርም) 1A (የቤት ኪራይ ኣለመክፈልን ያስመለከተ - የመኖርያ ቤት)

ተከሳሽን/ተከራይን የሚከሱበት ምክንያት የቤት ኪራይ ስላልከፈለ ወይም ስላልከፈለች ብቻ ከሆነ፣ ቅጽ (ፎርም) 1A መጠቀም ይኖርቦውታል። ለተከሳሽ/ለተከራይ ኪራይ ባለመክፈሉ የማቆም ማስጠንቀቅያ ፣ የማረምያ ወይም ቤቱን እንዲለቅ ማስጠንቀቅያ ቢሰጡም እንኳን፣ ቅጽ (ፎርም) 1A መጠቀም ይኖርቦውታል።

ቅጽ (ፎርም) 1A መቸ መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳዩ ምሳሌዎች፣

- ተከራይዎ የቤት ኪራይ ሳይከፍል በመቅረቱና ኪራይ ባለመክፈሉ ቤት እንዲለቅ የሚላክ ማስጠንቀቅያ የመቀበል መብቱን እንዳስረከብ በግልጽ በከራይ-ውል ውስጥ ከሰፈረ።
- ተከራይዎ የቤት ክራይ ሳይከፍል በመቅረቱ እርስዎ ለተከራዩ በ30-ቀናት ውስጥ ያልተከፈለውን የኪራይ ዕዳ እንዲከፍል የሚያሳስብ ማስጠንቀቅያ ከላኩ። እንዲሁም በማስጠንቀቅያ ዉስጥ *ሌሎች ምንም* የተጣሱ የኪራይ-ውሎች የሉም።

ናሙና፡ ቅጽ (ፎርም) 1A እነኝህን መመሪያዎች ይከተላል። ከዚህ ጽሁፍ ጋር በኣባሪነት የተያያዘው "ናሙና ፎርም 1A" ውስጥ በቁጥር የተጠቀሱት ሳጥኖች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመመሪያዎች ቁጥር ጋራ የሚገናኙ ናቸው።

1. L&T የጉዳይ ቁጥር። ፀሃፊው የጉዳይ ቁጥር ስለሚሰጡዎ ይህንን ቦታ ክፍት ይተዉት።

2. የከሳሹን ስም፣ ሙሉ ኣድራሻና እንዲሁም ዚፕ ኮድና የስልክ ቁጥሩን ታይፕ ወይም በጠራ የእጅ ጽሁፍ ይጻፉት። የፖስታ-ቤት የሳጥን ቁጥር እንደ ኣድራሻ መጻፍ የለቦትም። ጥቁር ቀለም ይጠቀሙ።

3. የተከሳሹን ስም፣ ሙሉ ኣድራሻና እንዲሁም የኣፓርትመንት ቁጥር፣ ስዊት ወይም የመሬትና ኣደባባይ ስም፣ ኩዋድራንትና (NE, NW, SE, or SW)
ዚፕ-ኮድ ታይፕ ያድርጉ ወይም በጠራ የእጅ ጽሁፍ ይጻፉት። ተከሳሹ በሌላ ኣድራሻ ማለት እርስዎ ለመውሰድ ከሚፈልጉት ቤት እንደሚኖር ካወቁና ኣድራሻውን ካወቁ፣ የተከሳሹን ወቅታዊ ኣድራሻ በዚህ የክስ ክፍል ውስጥ ይፃፉት። የተከሳሹን የስልክ ቁጥር ካወቁት እንዲጨምሩ ይገደዳሉ።

4. ስምዎን፣ ኣድራሻዎንና የስልክ ቁጥርዎን ይፃፉ። ከሳሽ፣ የከሳሽ ጠበቃ ወይም ክሱን የማጣራት ሥልጣን ያለው ወኪል መሆንን ለማመልከት ከሰወስቱ ሳጥኖች ኣንዱን ይምረጡ። የከሳሹ ወኪል ከሆኑ ከከሳሹ ጋር ያሎትን ግንኙነት ለከሳሹ ያስረዱ፣ ከሳሹ ድርጅት ከሆነ የሙያዎን መጠርያ ይጨምሩ።

5. ከንብረቱ ጋር ያሎትን ግንኙነትና ንብረቱን ለመውሰድ ያሎትን ሥልጣን ለማመልከት ከሰወስቱ ሳጥኖች ኣንዱን ይምረጡ። ኣከራይ ወይም የንብረቱ ባለቤት ከሆኑ መጀመርያውን ሳጥን ይምረጡ። የርስት-ንብረት ተወካይ ከሆኑና ንብረቱን ለመውሰድ የመጠየቅ ሥልጣን ካሎት የፍርድ-ቤት የውርስ ምርመራ ጉዳይ ቁጥር በተገቢው ሥፍራ ይጨምሩት። ኣከራይ፣ ባለንብረት ወይም የንብረቱ የግል ተወካይ ካልሆኑ ነገር ግን ንብረቱን የማስመለስ መብት ኣለኝ ብለው ካመኑ፣ በተሰጠው ቦታ ውስጥ የመጠየቅ ስልጣንዎን ያስረዱ።

6. ለማስመለስ የሚፈልጉትን ንብረት ትክክለኛ ኣድራሻ ታይፕ በማድግር ወይም በእጅ በግልፅ ይጻፉት። የኣፓርትመንት ቁጥር፣ ስዊት ወይም መሬትና ኣደባባይ፣ ኩዋድራንት (NE, NW, SE, or SW) እንዲሁም ዚፕ-ኮድ ይጻፉ።

7. በዚህ ክፍል ውስጥ ንብረቱዎን ለማስመለስ ሕጋዊ መብት እንዳሎት ለፍርድ ቤት ያስረዱ። ተከሳሹን/ተከራይን የከሰሱበት ምክንያት እርሱ/እርስዋ የቤት ኪራይ ባለመክፈሉ/ባለመክፈልዋ ስለሆነ ይህን ሳጥን ይምረጡ። የገንዘብ ብይን ባይፈልጉም እንዲሁም ለተከሳሽና/ለተከራይ የቤት ኪራይ ባለመክፈላቸው እንዲታረሙ/እንዲለቁ/እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ የሰጡ ቢሆኑም እንኳን ይህን ሳጥን ይምረጡ።

a. በዚህ ክፍት ቦታ ውስጥ የተከሳሽ/የተከራይ ጠቅላላ ድምር *የክራይ ዕዳ* ይጻፉ። በዚህ ድምር ውስጥ የመዘግየት ቅጣት ክፍያ፣ የፍርድ ወጪዎት፣ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎችን *ኣይጨምሩ*።

b. እና c. ተከሳሽ/ተከራይ ክራይ ለምን ያህል ግዜ እንዳልከፈሉ ይዘርዝሩ። ለምሳሌ ክራይ የሚከፈለው በመጀመርያ ወር ከሆነና ተከሳሽ/ተከራይ ፌብሩዋሪና ማርች ክራይ ካልከፈለ እርስዎ ፌብሩዋሪ 1, 2010 እስከ ማርች 31, 2010 ብለው ይጽፋሉ።.

d. ተከሳሽ/ተከራይ በሕግ ተገዶ በየወሩ መከፈል ያለበትን ኪራይ ይግለጹ። እዚህ ሂሳብ ዉስጥ የመዘግየት መቀጮ ክፍያና ሌሎችም ክፍያዎች *ኣይጨምሩ*።

e. የኪራይ ውሉ በመዘግየት ምክንያት እንዲከፈል የሚጠይቀውን መቀጮ ክፍያ (ካለ) ይዘርዝሩ።

f. ተከሳሽ/ተከራይ ለእርስዎ ያልከፈላቸው ሌላ ክፍያዎች ካሉ ይዘርዝሩ። እዚህ ሂሳብ ዉስጥ የፍርድ-ቤት ወጪዎችን *ኣይጨምሩ*።

g. በቁጠር (f) ለተዘረዘሩት ክፍያዎች ምክንያቶችዎን በግልጽ ያስረዱ።

h. ሊሎች ክፍያዎች በቁጥር (f) እንዲመዘገቡ ከፈለጉ በኪራይ-ውል ዉስጥ በየትኛው ኣንቀጽ እንደ ኪራይ እንደተጠቀሱ መግለጽ ይኖርቦታል። ሆኖም ንብረቱ የመንግሥት ድጎማ የሚያገኝ ወይም በኪራይ ቁጥጥር የሚተዳደር ከሆነ፣ ሌሎች ክፍያዎችን በቁጥር

(f) ዉስጥ የማስገባት መብትዎ ሊገደብ እንደሚችል ይረዱ። ሌሎች ክፍያዎችን በክስዎ ዉስጥ መጨመር በሚመለከት እርግጠኛ ካልሆኑ ከአከራይ-ተካራይ የመረጃ ማዕከል ወይም ከጠበቃ የሕግ ጠይቀው ያግኙ።

i. ከላይ የዘረዘሩዋቸውን የኪራይ፣ የመዘግየት መቀጮና ሌሎችም ክፍያዎች ደምረው ጠቅላላ ድምሩን እዚህ ያስፍሩ። ማንኛውም የፍርድ-ቤት ወጪ እዚህ ድምር ዉስጥ ኣይጨምሩ።

8. የሚመለከትዎትን ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ለተከሳሽና/ለተከራይ የቤት ክራይ ባለመክፈላቸው እንዲታረሙ፥ እንዲለቁ ወይም እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ ከሰጡ "ሕግ የሚያዘውን ፈጽመዋል" የሚለውን ሳጥን ይምረጡ። ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ በኪራይ-ውል ውስጥ ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብት ማስረከባቸው በግል ካወቁ፥ "እኔ እራሴ ውሉን ኣንብቤ ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ ኣስወግደዋል ..." የሚለውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ። ይህን ሳጥን ከመረጡ፣ ተከሳሽ/ተከራይ በውሉ ዉስጥ ማስጠንቀቅያ ኣንፈልግም ያሉበትን ኣንቀጽና ቁጥር ይጨምሩ። ተከሳሽ/ተከራይ ኪራይ ባለመክፈል እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብት ከውሉ በተለየ ሰነድ ከሰፈረ ሶስተኛውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ ሆኖም ሰነዱን ከክሱ ጋር ማያያዝ ይኖርቦታል።

9. ተከሳሽ/ተከራይ እንዲሁም/ወይም የጉዳዩ ንብረት ከፌዴራል ወይም ከኣካባቢ መንግስት ድጎማ የሚያገኙ መሆኑን/ኣለመሆኑን ላማመልከት ከሁለቱ ሳጥኖች ኣንዱን ይምረጡ። ንብረቱ ድጎማ ካላገኘ "ኣይደለም" የሚለውን መርጠው ወደ የሚቀጥለው ክፍል ይቀጥሉ። ተከሳሽ/ተከራይ እንዲሁም/ወይም የጉዳዩ ንብረት ድጎማ የሚያገኙ ከሆኑ "ኣዎን" የሚለውን መርጠው በኣንቀጹ ዉስጥ ያሉትን ጥያቀዎችን በሙሉ ይመልሱ። እንደድጎማ ቤቶች ለምሳሌ Housing Choice Voucher/Section 8 ወይም Department of Mental Health Voucher ፕሮግራሞች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

10. ይህን የክስ ክፍል በመሙላት፥ ፍርድ ቤቱ ምን ማድረግ እንዳለበት ለፍርድ ቤቱና ለተከሳሹ እያስታወቁ ነው።

a. የመጀመርያውን ሳጥን በመምረጥ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ከንብረት የሚያስወጣ ትእዛዝ እንዲሰጥ እየጠየቁ ነው። የኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) ግን ንብረትን የማስመለስን ክሶችን ብቻ ነው የሚመለከተው። ስለዚህ ተከሳሹ እንዲለቅ ካልፈለጉ ግን ጉዳዮትን በኣነስተኛ ክሶችና የዕርቅ ወይም የሲቪል ጉዳዮች (Small Claims and Conciliation or Civil Actions) የሚባሉ የፍርድ ቤት ቅርንጫፎች ፋይል ይክፈቱ።

b. ፍርድ ቤት ተከሳሹ ለእርስዎ ባልከፈለው የኪራይ ዕዳ የገንዘብ ብይን እንዲያደርግ ከፈለጉ ሁለተኛውን ሳጥን ይምረጡ። መፈረድ ያለበትን የገንዘብ መጠን በቀኝ በኩል ባለው ክፍት ቦታ ይግለጹ። የገንዘብ ብይን ኪራዩን ከተከሳሹ ለመጠየቅ ይረዳዎታል፥ ለምሳሌ ተከሳሹ በፈቃዱ ካልከፈለ ደሞዙን ማስያዝ ይቻላል።

c. ፍርድ ቤት ተከሳሹን በየወሩ የቤት ኪራይ ለፍርድ ቤት እንዲያስከፍለው ከፈለጉ ሶስተኛውን ሳጥን ይምረጡ። ጉዳይዎ በመጀመርያ የፍርድ ቀን ካልተፈጸመ ጉዳይዎ እስኪዘጋ ድረስ ገንዘቡ በልዩ ኣካውንት ይቀመጣል። (ፍርድ ቤት ማዘዝ የሚችለው የመጪውን ኪራይ ማለት ከመጀመርያ የፍርድ ቀን ጀምሮ ጉዳዩ እስከሚፈጸም ድረስ ያለውን ጊዜ እንጂ ያለፈውን ክራይ ኣይደለም)።

11. እርስዎ ክሱን ከፈረሙ በኋላ የሰነድ-ኣጽዳቂው ወይም የፍርድ ቤት ጸሓፊው ይህን ክፍል ይፈጽመዋል። የክሱ ሰነድ ያለኣንዳች ክፍያ በLandlord and Tenant Clerk ቢሮ ለጸድቅ ይችላል።

12. በክፍል 4 የተጠቀሰው ሰው ክሱን በኣከራይና ተከራይ ጸሓፊ ቢሮ (Landlord and Tenant Clerk's Office) በሚሰራ የሰነድ-ኣጽዳቂ ወይም ጸሓፊ ፊት በመቅረብ በዚህ ቦታ መፈረም ኣለበት።

13. በክፍል 4 እንዲሁም በክፍል 12 በፊርማ መስመር ላይ ስሙ የተጠቀሰው ሰው የሚፈርመው ድርጅትን በመወከል ከሆነ፥ ይህ ሰው ማዕርጉን/ማዕርጉዋን በተሰጠው መስመር ላይ መጨመር ኣለበት/ኣለባት(ለምሳሌ ፕረዚደንት፥ ገንዘብ-ያዥ፥ የንብረት ኣስተዳዳሪ)።

14. ይህ ኣስፈላጊ ነጥብ እርስዎን ሊመለከት ይችላል። በ District of Columbia ባለስመ-ጥሩ ጠበቃ ካልሆኑ፣ ጉዳዩ ኣንዲቀጥል ከመጠየቅ በስተቀር ሌላ ሰውን በመወከል በኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) በመቅረብ ጉዳዮችን ለመፈጸም ከሞከሩ ያለፍቃድ የሕግ ሥራ እንደሰሩ ሊቆጠር ይችላል።

15. በጠበቃ የሚወከሉ ከሆኑ፣ እሱ/እስዋ የጥብቅና ቁጥርና የኢሜል ኣድራሻ በመጨመር ይህን ክፍል መሙላት ኣለበት/ኣለባት። በጠበቃ የማይወከሉ ከሆኑ ይህን ክፍል በራስዎ መረጃ ይምሉት። ጠበቃ ካልሆኑ የጠበቃ ሞያ ቁጥርና ኢሜይል (Unified Bar No. and Email Address) የሚለውን ቦታ ክፍት ይተዉት። የክሱን ማጣራት የሚለውን ክፍል ከከሳሽ የተለየ ሰው ከሞላው፣ ከሳሽ ወይም የከሳሽ ጠበቃ ክሱን በዚህ ክፍል ዉስጥ መፈረም ኣለባቸው።

16. ይህን ክፍል ክፍት ይተውት። ክሱን ሲያቀርቡ ጸሓፊው የሚፈቀደውን ጠቅላላ ወጪ እዚያ ውስጥ ይጽፈዋል።

# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሲቪል ክፍል

## የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ

510 4th STREET, N.W., Building B, Room #110, Washington, D.C. 20001 የስልክ ቁጥር (202) 879-4879

የጉዳይ ቁጥር LTB______1___________

| | |
|---|---|
| ____________2______________________ | ከ _____________________3____________________ጋር |
| ከሳሽ (ሾች) | ተከሳሽ (ሾች) |
| ________________________________ | ________________________________ |
| ኣድራሻ (ፖስታ ሳጥን ያልሆነ | ኣድራሻ |
| ________________________________ | ________________________________ |
| ከተማ ስቴት ዚፕ ኮድ | Washington, D.C. |
| ________________________________ | ________________________________ |
| ስልክ ቁጥር | ስልክ ቁጥር (*ከታወቀ*) |

## የቤት ንብረት በእጅ መያዝን ያስመለከተ የተረጋገጠ ክስ -- ቅጽ (ፎርም) 1A

### (የቤት ኪራይ ኣለመክፈል በተመለከተ- የመኖርያ ቤት)

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ss:

1. እኔ *(ስም፣ኣድራሻ፣ እንዲሁም ስልክ ቁጥር)* _______________4_______________ እዚህ ክስ ውስጥ ስለቀረቡት ነጥቦች ግንዛቤ እንዳለኝና ከሳሽ ወይም የከሳሽ ጠበቃ ወይም የከሳሽ ወኪል በመሆን ይህን ክስ ለማጣራት ስልጣን እንዳለኝ እምላለሁ ወይም ኣረጋግጣለሁ። ይህ እውነት ሆኖ ካልተገኘ በውሸት ምስክርነት እከሰሳለሁ። ከከካሹ ጋር ያለኝ ግንኙነት *(ያስረዱ፣ ከሳሽ ኮርፖረሽን ከሆነ ሹመትዎን ይጨምሩ*_______________________________

2. 5_ከሳሽ፡ ኣከራይ ወይም ባለቤት ነው፣ ወይም የርስትና ንብረት የግል ተወካይ ሆኖ በጉዳይ ቁጥር____መሰረት ተሹሙዋል ንብረቱንም በእጅ የማድረግ ስልጣን ኣለው፥ ወይም D ኣከራይ፣ ባለቤት ወይም የግል ወኪል ኣይደለም፥ ነገር ግን በእጅ ለማድረግ የመጠየቅ መብት ኣለው ምክንያቱም (*ኣስረዳ*)።_______________________

3. ከሳሽ በ_______________6______________________ዋሽንግተን ድሲ የሚገኘውን ንብረቱን በእጅ ማድረግ ይፈልጋል። ንብረቱ በተከሳሽ ማለት መብት በሌለው ተከራይ እጅ ይገኛል። ከሳሽ በእጅ ማድረግ የሚፈልገው ተከሳሽ $_______ ድምር የቤት ክራይ ከ________እስከ ባለመክፈሉ ነው። ወርሃዊ የክራይ 7ክፍያ$____a___ነው። ዘግይቶ ለሚከፍል ውሉ $___b____መቀጮ ይፈቅዳል። ከሳሽ ሌሎች የ_c___ ክፍያዎችን በኣንቀጽ ____ የኪራይ ውል ውስጥ እንደ ኪራይ የተቆጠሩ(*ሉን በሁሉም የፍርድ ቤት የቀጠሮ ቀን ይዘዉት ይምጡ*) ለ______ (*ኣስረዳ*) ለዚህ ከድጎማ ና የኪራይ ቁጥጥር ነፃ የሆነ ንብረት ይፈልጋል። ጠቅላላ ከሳሽ የሚገባው $_______-________።
 8የመልቀቅያ ማሳሰብያ፡ ሕግ ኣንደሚያዘው ተልኮ ነበር፣ ወይም እኔ ዉሉን በደንብ ኣንብቤው ተከሳሽ በግልፅ በኣንቀጽ_____ቁጥር____የመልቀቅያ ማሳሰብያ የመቀበሉን መብት ኣስረክቧል፥ ወይም ተከሳሽ በግልፅ በሌሎች ሰነዶች ያንን መብት ኣስረክብዋል(*ሰነድ ኣያይዝ*)።

4. 9ከሳሽ በእጅ ለማድረግ የሚፈልገው ንብረት ኪራይ በፌደራልና ወይም በኣካባቢ መንግስት ድጎማ ስር ነው ወይ? ኣዎን/ኣይደለም? ንብረቱ ድጎማ የሚያገኝ ከሆነ ለሚከተሉት ጥያቅርዎች መልስ ይስጡ፡
   ከተከራዩ በየወሩ ስንት የኪራይ ገንዘብ (ካለ) ይጠበቃል? $_________
   ከድጎማው ፕሮግራም በየወሩ ምን ያህል ወደ ኪራይ ይሄዳል? $_________
   በክሱ ውስጥ ለሆነ ወር ያልተከፈለ ተብሎ የተመዘገበው፣ ለዚያ ወር ከተከራይ የክራይ ድርሻ በላይ ነው ወይ? D ኣዎን D ኣይደለም።
   የድጎማ ፕሮግራም የሚገባውን የክራይ ድርሻ ሳይከፍል የቀረብት ጊዜ በዚህ ጉዳይ ከተዘረዘሩት ወራት ውስጥ ኣለ ወይ? D ኣዎን D ኣይደለም።

ስለዚህ ከሳሽ ፍርድ ቤትን የሚጠይቁት *(የሚመለከትዎትን በሙሉ ይምረጡ)*

10 የተጠቀሰውን ንብረት በእጅ ማድረግና በፀሓፊው የተቀረጠው ወጪ እንዲከፈል የሚል ፍርድ።
ለክራይ፣ እንደ ክራይ ለተቆጠሩ ክፍያዎችና የመዘግየት መቀጫዎችን ያጠቃለለ የገንዘብ ፍርድ በድምር $___።
ጉዳዩ እስከሚፈረድ ድረስ የወደፊት ክራይ በሙሉ ለፍርድ ቤት የምዝገባ ክፍል እንዲከፈል የሚያዝ የመከላከያ ፍርድ።

በፍቃዱ ከእኔ ፊት ቀርቦ ፈርሞ ቃለ መሃላውን የፈፀመው በዚህ____ዕለት የ_______ 20_______ 12____________________________________
11 ከሳሽ/የከሳሽ ጠበቃ/የከሳሽ ወኪል ዕለት

____________________ ________________________ 13_________________________________
የሰነድ ኣጽዳቂ ስልጣኔ የሚቃጠልበት ጊዜ የፈራሚ ሰም ሹመት (*ካለ*)

**14 ኣስፈላጊ ማሳሰብያ ለተሳታፊዎች፣** የይግባኝ ፍርድ ቤት ደንብ 49፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሲቪል ደንብ 101 እንዲሁም የኣከራይና ተከራይ ደንብ ቁጥር 9 ያለፍቃድ የጥብቅና ስራ መስራትን ይከለክላል። ማንኛውም ሰው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ስመ-ጥሩ ጠበቃ ያልሆነ፣ እርሱ ወይም እርስዋ ሌላ ሰው በመወከል በኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) በመሄድ ጉዳዩ እንዲቀጥል ለመጠየቅ ብቻ ካልሆነ፣ ያለፍቃድ የጥብቅና ስራ ዉስጥ እንደተሰማራ መገንዘብ ኣለበት።

15________________________________________ ________________________________________
ከሳሽ/የከሳሽ ጠበቃ የሕግ ሙያ ቁጥር የፍርድ ቤት ፀሓፊ

________________________________________
ኣድራሻ ዚፕ ኮድ

________________________________________ የዚህ ክስ ወጪዎች እስከዛሬ ድረስ $______16______ ናቸው።
የስልክ ቁጥር የኢሜይል ኣድራሻ (ለጠበቃ ብቻ)

የኣማርኛ ትርጉም ለማግኘት (202) 879-4828 ይደውሉ